# መልስ ለክንፉ አሰፋ – ኢሳያስ አፈወርቂን በጨረፍታ ብሎ በጻፈው ላይ – ግርማ ካሳ

March 4, 2015 -

ጋዜጠኛ ክንፉ አሰፋ፣ ከፕሬዘዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ኢሳት ባደረገው ሶስት ክፍል ቃለ ምልልስ ዙሪያ፣ ያቀረበዉን ጽሁፍ አነበብኩ። ግሩም ጽሁፍ ናት። ከታች ምክንያቴን ከማስረዳባት አንድ ነጥብ በስተቀር የተጻፈዉን በሙሉ እጋራለሁ። እጋራለሁ።

ክንፉ አቶ ኢአሳያስ ላይ ትንሽ ጠንከር ብሏል። እኔ ደግሞ ክንፉ ያስቀመጣቸው ነጥቦች ትክክል ቢሆኑም፣ አቶ ኢሳያስ ፖሊሲዎቻቸውን እንዲያሻሽሉ ኢንጌጅ ማድረጉ ሊጠቅም ይችላል የሚል ሐሳብ ይዤ መጥቻለሁ። ምነው ከሕወሃት ጋር መነጋገር ያስፈለጋል ስንል አልነበረም እንዴ ? ታዲያ ከሕወሃት ጋር ለመነጋገር ከፈለግን ለምን ከሻእቢያ ጋር አንነጋገርም ?

አንድ ቃለ መጠይቅ ከሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይችላል። በኤርትራ የነበረዉን እና ያለዉን ኢሰብአዊ የሙብት ረገጣ ፕሬዘዳንቱ ቢክዱም፣ የተናገሩት ሁሉ ዉሸት ነው ማለት አይቻልም። ስለዚህ ያለፈዉን ለታሪክ ትተን ወደፊት ምን ማድረግ ይቻላል በሚለው ላይ ትኩረት መስጠቱ ጠቃሚ ይመስለኛል።

የኢሳት ጋዜጠኞች በግልጽ እንደጠየቁት ሻእቢያ በኢትዮጵያዉያኖች ዘንድ በጣም ይጠላል። በኤርትራ የሚታገሉ እንደ ግንቦት ሰባት ያሉ ድርጅቶች ከሻበኢያ ጋር በመስራቱ ዙሪያ ኢትዮጵያዉያንን ለማሳመን በጣም የሚቸግራቸው ይመስለኛል። ሆኖም ከባድ ቢሆንም የማይቻል ግን አይደለም። በተለይም ከኤርትራ መንግስት አዎንታዊ ትብብር ከተገኘ።

ክንፉ አሰፋ እንዳስቀመጠው «ያለፈውን እንተወው እና ወደፊት ምን ማድረግ ይገባናል የሚለው ላይ ማተኮር ነው ያለብን። ….ድንበር ጉም ነው" ፕሬዘዳንት ኢሳያስ ፣ ኤርትራዉያኖች ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነትና ዝምድና የበለጠ ጥሩ እንዲሆን ፍላጎት እንዳላቸው በግልጽ አስቀምጠዋል። ይህ መልካም ነገር ነው። ሆኖም አብሮ ለመስራት፣ ለሙተባበር ሙተማመን ያስፈልጋል።

ክንፉ በዋናነት፣ የኤርትራ መንግስት በኤርትራ ያሉ የታሰሩ ኢትዮጵያዉያንን መፍታት እንዳለበት ጠየቋል። ይሄ የኔም ሆነ የብዙዎች ጥያቄ ነው ። «ስለ ኢትዮጵያ መቆርቆር ከዚህ ይጀምራል። እነዚህ ወገኖቻችንን ነጻ ካደረጓቸው በኋላ ኢትዮጵያውያንን ለውይይት ቢጠሩ አንድ ነገር ነው። በትንሹ ያልታመነ፣ በትልቁ አይታመንምና» ሲል ነው ቁልፍ ነጥብ ክንፉ ያስቀመጠው።

በኤርትራዉያን ላይ የሚደርሰው የሰብአዊ ሙብት ረገጣ ግን ክንፉን ብዙ ያስጨነቀው አይመስለም። «ስለ ኢሳያስም ሆነ ስለ ኤርትራ ጉዳይ እኛ አያገባንም። አምባገነንነታቸው የኛ ጉዳይ ላይሆን ይችላል። የዚያች ሃገር ጉዳይ "ኢትዮጵያዊ አይደለንም" ብሎ 99.9 በሙቶ ድምጽ የሰጠው ህዝብ ጉዳይ ነው» ሲል ነው የጻፈው።

ይህ ሎጂክ ትክክል አይመስለኝም። ከአምስት አሙት በፊት ህወሃት/ኢህአዴግ በ 99.6% ድምጽ አልነበረም እንዴ አሸነፍኩ ያለው ? ነጻና ፍትሐዊ ባለሆነ፣ የተለየ ዉሳኔ ከተወሰነ ምን ሊከተል እንደሚችል በታወቀበት ሁኔታ 99.9% የሚሆነው ሕዝብ ከኢትዮጵያ ለመለየት ፈልጎ ነበር ማለት ይቻላልን? እንደዉም ቢያንስ ሐማሴን፣ አኩሎ ጉዛይ እና ከመረብ በላይ ያሉትን እንተዋቸውና፣ ደንከሊያ ያሉ አፋሮች መገንጠልን ይመርጣሉን ? አይመስለኝም። እና የተባለዉን አምነን 99.9 የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያን አይፈለግም ነበር ማለት ትልቅ ስህተት ነው። በወቅቱ የነበረው ፖለቲካ ሰለባ መሆን ነው።

እንደዉም ጦቢያ የምትባል መጽሄት ላይ፣ ኢሳያስ አፈወሪቂ ራሱ ፣ የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ግንኙነት በፌዴሬሽን ይሁን በኮንፌዴሬሽን እንዲሆን ፍላጎት እንደነበረው፣ ተዘግቦ እንደነበረ ሰዎች ሲናገሩ ሰምቻለሁ። የመሐሉን ሃገር ሃብት ለብቻቸው ለመጠቀም ሲሉ፣ ሕውሃቶች በሴራ ኤርትራዊያኖችን ከኢትዮጵያ እንዳስወገዱ ነው መረጃዎች የሚይሳዩት። በዚህ ረገድ በጣም እንደተሳካላቸው እያየን ነው። አንድ ወቅት " **The Gloom of Meles and the Doom of Issayas**" በሚል የት እንደነበረ አላወቅም ጽሁፍ አንብቤ ነበር። እንደ ጽሁፉም የስሜን ማእከል አስመራ ሳትሆን መቀሌ ሆናለች። ድሮ ከአምቦ፣ ደብረ ብርሃኑ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጣው ከትግራይ ወደ አስመራ ነበር የሚመጣው። አሁን ተገላቢጦሽ ሆኗል። (ኤርትራ ከኢትዮጵያ ባትለይ ኖሮ፣ እንኳን የነበረው አንዱ ዩኒቨርሲቲ ሊዘጋ፣ ሌሎች ተጨማሪ አምስት ዩኒቨርሲቲዎች ይገነቡ ነበር)

ወደ መጀመሪያው ሐሳቤ ልመለስና፤ ለዉይይት ያህል፣ ክንፉ እንዳለው 99.9% ኤርትራዊያን ነጻነትን በርግጥ ፈልገው ነበር ብለን ብንቀበል እንኳ፣ የኤርትራዊያን ጉዳይ ሊያገባን ይገባል። የሰው ልጅ፣ የሰው ልጅ ነው። የትም አገር ዜጋ ይሁን በሰው ልጅ ላይ የሚደርስ ግፍ እኛንም ሊያመን ይገባል። አለበለዚያማ ለምንድን ነው በየዉጭ አገራቱ ነጮች በኢትዮጵያ ስለሚደርሰው ግፍ እንዲቆረቁርልን ሰልፎች የምንወጣው ?

ስለዚህ በኤርትራ ያሉ ኢትዮጵያዉያን እስረኞችን መፍታት ብቻ ሳይሆን፣ የኤርትራ ህዝብን ሙብት ሻእቢያ ማክበር መጀመር አለበት። ወጣቶች እየታፈሰ ወደ ዉትድርና መላኩ መቆም አለበት።

ከኤርትራ ጋር እንሰራለን የሚሉ ድርጅቶችም፣ አስመራ ሄደው መንቀሳቀሳቸዉን ልንቃወም ባንችልም፣ ሙብታቸው ቢሆንም፣ ያለ ኢትዮጵያዉያን ድጋፍ ብዙ መግፋት እንደማይችሉ ያጡታል ብዬ አላስብም። በመሆኑም ከነኢሳያስ ጋር በሚያደርጉት ዉይይቶች፣ የኢትዮጵያ እስረኞች ጉዳይና በኤርትራ የሰብአዊ ሙብት መከበር ዙሪያ መጠየቅ

መቻል አለባቸው። ጋዜጠኞች፣ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን አማኞች መፈታት አለባቸው።
በነዚህ ጉዳዮች ማሻሻያዎችን ለማድረግ እነ ኢሳያስ ካልፈለጉ፣ እንዴት ነው ታዲያ "ወያኔ" እያሉ አራቲ ኪሎ ያሉትን ለመተቸት የሚችሉት ? ለሕዝባቸዉስ ያለሆኑ እንዴት ለኢትዮጵያዉያን ይሆናሉ ? ግፍ እየተፈጸመበት ካለው የኤርትራ ሕዝብ ጋርስ መጣለት አይሆንምን ?